# የመምህር የየኔሰው ገብሬ መስዋእትነት
# የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) የትግልና የመስዋእትነት ታሪክ አካል ነው !!

**በስደት የኢመማ አደራጅ ጊዜያዊ ኮሚቴ**

የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1941 ዓ.ም የተመሰረተ አንጋፋ የሙያ ማህበር ነው። አመሰራረቱም የመምህራንን ጥቅምና የሙያውን ክብር ለማስጠበቅ ያለመ ቢሆንም በሂደት በነባራዊ ሁኔታዎች ላይ በማተኮር በሕብረተሰቡ እድገት ላይ ጋሬጣ የሆኑ የመንግስት ተግባራትን ለይቶ በማውጣት ፍትህ ተጓደለ ፣ ሕዝብ ተበደለ በሚል ተቃውሞ ታግሎ ማታገልን መርሆ አድርጎ ተንቀሳቅሷል።በአጼው ስርአት ማህበሩ ህጋዊ ፈቃድ ለማግኘት ብዙ አመታት ፈጅቶበታል። ማህበሩ መስዋእትነት መክፈል የጀመረው ገና ከውልደቱ እንደሆነ የትግል ታሪኩ ይመሰክራል።

በ1966 ዓ.ም ሕዝባዊ አብዮት ሲቀጣጠል በወቅቱ በትምህርቱ ዘርፍ ሴክተር ሪቪዩ በመባል የተቀየሰውን የትምህርት ፓሊሲ በመቃወምና ሌሎች የዲሞክራሲያዊ መብቶችንም አካቶ የሕዝቡን አመጽ መልክ በማስያዝ ረገድ መምህራንና ማህበራቸው ኢመማ ታሪካዊ ድርሻቸውን ተወጥተዋል።

ከዘውዱ ስርአት መገርሰስ በኋላም በወታደራዊ ደርግ መንግስት ኢመማ በአባላቱም ሆነ ባጠቃላይ በሕዝቡ ላይ የሚደርሰውን አፈናና ጭና መረን ከመልቀቁ በፊት እንዲገታ ገና ከጅምሩ በትግሉ ተጋፍጧል። በዚህም በ1967(እ.ኢ.አ) ዓ.ም ክረምት ወራት በጅማ ከተማ ላይ በተካሄደው የማህበሩ ጉባኤ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም፣ መለዮ ለባሹ ስልጣኑን ለሕዝቡ ያስረክብ፣ የዲሞክራሲ መብቶች ይከበሩ ብሎ አቋሙን በማሳወቁና ሕዝባዊ ጥያቄ በማቅረቡ በርካታ ቆራጥ የማህበሩ መሪዎችና አባላት የእስራት፣ የግርፋት፣ የግድያና ከአገር የመሰደድ ሰለባ ሆነዋል። የደርግ ስርአት ማህበሩን በኢሰፓ ፓርቲ አምሳያ በመቅረጽ የአባላቱንና የማህበሩን ህልውና የሚፈታተኑ ሁኔታዎች በመፈጠራቸው ትግሉን ውስብስብና መስዋእትነት የሚያስከፍል አድርጎት ቆይቷል።

ከደርግ ስርአት መውደቅ በሁዋላ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበራቸውን ከዘር፣ ከሃይማኖት፣ ከጾታ አድልዎ የጸዳ፣ የማንም ፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም ማራመጃ ያልሆነና የመንግስት ጣልቃ ገብነት የማይኖርበት ነጻ የሙያ ማህበር እንዲሆን በሚያስችል መሰረት ላይ እንዲቆም የጋራ እምነትና መርሆ ተደርጎ ተወስዶ በማስከተልም አባላት በዲሞክራሲያዊ አግባብ በመረጧቸው መሪዎች የሚንቀሳቀስ ሆኖ ከመሰረታዊ እስከ አገር አቀፍ ተዋቅሮ ስራውን ጀመረ። በሂደቱም የመደራጀትና የመደራደር መርሆዎችንና መብቶችን በመጠቀም ከመላው ያገሪቱ ክፍሎች ከመምህራን ከቀረቡ አያሌ የሙብትና የብሶት ጥያቄዎች ተጨምቀው 20 ጥያቄዎች ለወያኔ የሽግግር መንግስት ቀረቡ።

እዚህ ላይ አንድ አሳዛኝ ክስተት ተፈጠረ። "ድመት መንኩሳ አመሏን ላትረሳ" እንዲሉ ወያኔ ከመነሻ እስከመድረሻው እጁ በንጹሃን ደም የተነከረ፣ በዘረኝነት አባዜ የሰከረ፣ ጸረ-ኢትዮጵያዊነት ሆኖ ሳለ ዲሞክራሲን መመሪያዬ አድርጌአለሁ እያለ በውሸት እየማለ ጸረ-ዲሞክራሲያዊነቱንና ጸረ-አንድነቱን በተግባር እያስመሰከረ ቀጠለ። እንደፖለቲካ አጀንዳው የኢትዮጵያን መምህራን በጎሳ ላይ በተሞረኮዘ የኦሮሞ መምህራን፣ የአማራ፣ የአፋር . . . ወዘተ ማህበር በሚል ጎሳን መሰረት አድርገው እንዲደራጁና ወያኔ በቀደደው ቦይ እንዲፈሱ ለመድረግ ጥሯል። ኢመማ ግን ይህን አካሄድ አጥብቆ በመቃወሙና በመታገሉ ወያኔ መምህራን በየደረጃው መርጠው የሰየሟቸውን መሪዎች በማሰር፣ ከስራ በማባረር፣ ህገወጥ ዝውውር በመፈጸም ወከባውን አጠናከረ። በመምህራኑ ሕጋዊ ተወካዮች ምትክ በ1985 ዓ.ም በያሬድ የሙዚቃ ት/ቤት ካድሬ መምህራንንና ከየክልሉ በመምህራን ስም የኮር አባላትን በማሰባሰብ በሻቢያው አባልና ወኪል በአቶ ዮሃንስ ሃጎስ የሚመራ ተለጣፊ ማህበር ያለብዙሃኑ መምህራን እውቅና ውጭ አቋቋመ።ይህ እንዳለ ሆኖ በመሪ ድርጅታቸው በኢመማ አማካይነት ላቀረባቸው የሙብት ጥያቄዎች እንደ መንግስት ተቋም ተቀራርቦ መወያየትና ችግሮችን በመደራደር መፍታት ሲቻል እንደ ስልጣን ተቀናቃኝ ባላንጣ በመቁጠር በአይነቱ የበዛና የከፋ ርምጃ መውሰድን አማራጩ አደረገ።

መምህራን የሙብትና የብሶት ጥያቄዎች ከማቅረባቸው በተጓዳኝ የትምህት ጥራትንና አቅርቦትን ለማስጠበቅ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጡት ብሔራዊ ጉዳያቸውና ሙያዊ ግዴታቸውም ስለሆነ በዚህ በኩልም የሚያቀርቧቸው ገንቢ ሃሳቦችና እውነታዎች ወያኔ/ኢህአዴግ ለሚያራምደው አደንቁረህና ከፋፍለህ ግዛ አላማ የሚጣጣሙ አልነበሩም። በመሰረቱ

ሕዝባዊ የትምህርት ፖሊሲ ቀጣይነት ባለው መልክ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደ አገሪቱ የእድገት ደረጃ የሚሻሻል እንጂ መንግስት በተቀየረ ቁጥር አብሮ የሚቀየር አይደለም። ያለመታደል ሁኖ ደርግ የአጼውን በመሻር የራሱን የትምህርት ፖሊሲ አዘጋጀ፡ ወያኔም እንዲሁ በጎሳ ላይ የተመሰረተ የትምህርት ፖሊሲ በመንደፍ አንድ ትውልድ ገድሏል። ኢመማ ይሄንን የዘረኞች የትምህርት ፖሊሲ ገና ከጅምሩ በጽናት ታግሏል። ለዚህም አባላቱ ከፍተኛ መስዋእትነትን ከፍለዋል።

የትምህርት ጥራት በሚመለከት በዚህ አምባገነን መንግስት ያገዛዝ ዘመን የተፈጸመው እኩይ ተግባር አንድ ትልቅ መድበል የሚወጣው ስለሆነ በዚህ ርእስ ብዙ ነጥቦች ማካተት ባይቻልም አንኳር አንኳሮቹን ከመላጎደል ለመጥቀስ ይሞከራል።ወያኔ በነፍጥ ወደ ስልጣን በወጣ ማግስት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የትምህርት ጥራት ይታገላሉ፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት እምነታቸው የጸና ነው የሚላቸውን፡ ለአካዳሚ ነጻነትም ይሟገታሉ ብሎ የጠረጠራቸውን ምርጥ የአ.አ. ዩኒቨርስቲ 42 መምህራንን አባሯል። እነዚህን አገሪቱ ያፈራቻቸውን ብርቅዬ ምሁራንን ሲያባርርና "በችሎታ ማነስ ተወግደዋል" የሚል የለበጣ ቅጥያ ስም አውጥቶላቸዋል። የትምህርት ውድቀት ጥንስስ ከዚህ ወቅት ይጀምራል። በአሁኑ የትምህርቱ ጥራት መውደቅ ከታችኛው ርከን ጀምሮ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ከድጡ ወደማጡ ሆኗል። በመጨረሻም ራሱ ወያኔ የትምህርቱን መውደቅ እየሸፋፈነ መኖር ስላልቻለ ዘግይቶም ቢሆን፣ እውነቱ እየመረረው ቢሆን ውድቀቱን በአደባባይ አምኗል። የማስተካከያ እምጃ ለመውሰድ ግን ፈቃደኛ አልሆነም።

በዚህ ጽሁፍ ቀደም ሲል የተገለጸውን የአምባገነኑ አገዛዝ የማን አለብኝ ርምጃ ሕዝቡ የሚያውቀው ቢሆንም ተጨማሪ ማሳያ ማቅረብና ማስታወስ እስከ አሁን ይህን ሁሉ ጉድ አስተናገድን ከእንግዲህስ ምን መደረግ አለበት ብሎ ለማሰላሰል ይረዳል እንላለን። በዚህ የጭቆናና የአፈና 20 አመታት አገዛዝ የኢትዮጵያ መምህራንና ማህበራቸው ኢመማ የከፈሉት መጠነ ሰፊና አሰቃቂ መስዋእትነት በእጅጉ ከገደብ በላይ ነው። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በአንድ ጊዜ 42 መምህራን እንደተባረሩ ሁሉ የኢመማ ግንባር ቀደም ደጋፊዎች በመሆናቸው 62 መምህራን ሌሎች 16 መምህራን በሕዝባዊ ስብሰባዎች የወያኔ የፖለቲካ አካሄድ ትክክል ያለመሆኑን በአደባባይ በመጋፈጣቸውና በይስሙላ ምርጫዎች ባስመራጭነትና በታዛቢነት ተመድበው ወያኔ አጭበርብሮ እንዲያሸንፍ ሽፋን ባለመስጠታቸው ባጠቃላይ 78 መምህራን ከደቡብ ወሎ ደሴ ከተማ ወደ ገጠር ተበትነዋል።

እጅግ የሚያሳዝነው ሚስት ከተማ ቀርታ ባል ወደገጠር በመሄዱ ትዳር ሊፈርስ ቤተሰብ ሊበተን ነው ብለው ላመለከቱ የወቅቱ ባለስልጣን መልስ ባልም ሚስትም እዚያ አለ የሚል ሆኖ እስከ አሁን በቁጭት የሚዘከር ጋጠወጥነት ከመሆኑ ባሻገር ኤድስ ወገኖቻችንን በሚያጭድበት ጊዜ ዝሙትን የሚያበረታቱ የወያኔ ቅምጥል ባለጌዎችንም ማንነት አሳውቋል። ከነዚህ መምህራን መካከል በጤንነት መታወክ ሳቢያ ከሆስፒታል እንዳይርቅ የሃኪም መረጃ ያለው አንድ መምህር ይሙት በቃ እንደተፈረደበት ሁሉ የዝውውሩ ሰለባ ሆኗል። እንዲሁም ሌላው መምህር በደሴ ሆስፒታል የ 8 ሃኪሞች (ቦረድ)ፊርማ ያለበትና ከአዲስ አበባ ጳውሎስ ሆስፒታል የ 4 ሃኪሞች ፊረማ ያረፈበት መረጃ አቅርቦ አቤቱታ ቢያሰማ ሰሚ በማጣቱ በረሃብ ከመሞት ይሻላል ብሎ ወደተመደበበት አውራጃ ለመሄድ ተገዷል፡; ይህን እንደናሙና አነሳነው እንጂ በአገሪቷ በመላ የደረሰ ኢፍታዊ ርምጃ ነበር። በተጨማሪ ማስረጃነትም በ1992 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ ወቅት በደቡብ ኢትዮጵያ ሐዲያ ዞን የምርጫ ታዛቢዎችና አስመራጮች የነበሩት መምህራን ላይ የግዴታ ዝውውር፡ እስር፡ ማፈናቀል አስከትሎ የወያኔ መደበኛ ጦር በመምህራንና በሌሎችም የህብረተሰቡ ቤተሰቦች ላይ በተለይ ሴቶችን አስገድዶ በመድፈር የጾታ ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል። ገጠርም አካባቢ ላይ የሰፈረው ሕዝብን ለማሸበርና በምርጫ አሸንፌአለሁ ብሎ ዝም ለማስባል ነበር። ለዚህ ለመምህራን ጥቃት መንስኤው ወያኔ እንዲመረጥ ፈቃደኛ አለመሆናቸውና ለሃቅ መቆማቸው ብቻ ነበር። ከዚሁ ከደቡብ ክልል ሳንወጣ ወያኔ በፈጠረው የተዛባ የትምህርት ፖሊሲ "ወጋጎዳ" የሚል ማስተማሪያ ሳይሆን ማደናገሪያ ቋንቋ ፈጥሮ በትምህርቱ ስራ ላይ ከፍተኛ ችግር በማስከተሉ የሰሜን አሞ ሕዝብ በተለይም ወላይታ ላይ አመጽ ተነስቶ 42 ሚሊዮን ብር ወጭ የተደረገበት መጽሀፍት ጋየቷል።

ህጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ በተባበሩት መንግስታት በዩኒስኮ ቻርተር የጸደቀ ቢሆንም ወያኔ የክልል ቋንቋ እንደ ግዴታ አድርጎ በአንዳንድ ከተሞች ለምሳሌ ናዝሬትን በመሳሰሉት ከክልሉ ቋንቋ ውጭ ባፍ መፍቻ ቋንቋ የሚናገሩና የሚግባቡ አፍ ባልፈቱበት የክልል ቋንቋ እንዲማሩ ጫና ተደርጎባቸዋል። በዚህ አቤቱታና ተቃውሞ በርካታ መምህራን ሰለባ ሆነዋል።እዚህ ላይ ልናጤነው የሚገባ ጉዳይ ቢኖር በመምህራንና በኢመማ ላይ ይደርስ የነበረው ውርጅብኝ የሙያና የዜግነት ግዴታ ለመወጣት ፍትህ ርትእ ለሕዝብ፡ ዲሞክራሲ ያለአድልኦ፡ የትምህርት ጥራት ይጠበቅ፣የትምህርት ፓሊሲው አምራችና ተመራማሪ ትውልድ እንዲያዘጋጅ ሆኖ ይቀረጽ በሚል አካልና ነፍጥ ባነገበ ሃይል መካከል ሆኖ እስከካሁን

ደርሷል፡ አልተገታም። ትግሉም መስዋእትነቱም ቀጥሏል። ወያኔ/ኢህአዴግ መምህራንን ቀደም ሲል በተገለጹት ኢፍትሐዊ እርምጃዎች ማዋከብ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባለፈ ብዙ ግፍ ሲሰራ ተስተውሏል። ማፈናቀል፡ ማሰርና ማሰቃየት አልበቃ ብሎት ታጣቂዎችን አሰማርቶ ግድያን ፈጽሟል። የአቶ አሰፋ ማሩን በአውራ ጠራራ ግድያ ያስታውሷል። የማህበሩን ፕሬዘዳንት ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት በፈጠራ ወንጀል ተከሰው ከ15 አመት እስራት ፍርድ በአለም አቀፍ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ጫና፣ በመምህራን ያላሰለሰ ትግልና በቀሪዎች የአመራር አባላት ጥንካሬና አይበገሬነት ከ6 አመት እስራት በኋላ ሊፈቱ ችለዋል።

እውነቱን ለመናገር ከሆነ መምህራንና ማህበራቸው ኢመማ ለወያኔ የጎን ውጋት ሆነውበት እንደቆዩ የራሱ ባለስልጣናትም “የኢትዮጵያን የጦር ሰራዊት ከማፍረስ(ከመበተን) በፊት ኢመማን ማፍረስ ነበረብን” እስከማለት ደርሰው ነበር። ወያኔ እያሰረም፡እያሰቃየም፡እየገደለም፡ ለስደት እየዳረገም ትግሉ ቀጥሎ 1997 ዓ.ም ድረስ ዘልቋል። ይህ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆ ብሎ ተነስቶ የወያኔን አገዛዝ ይብቃ፡ ድምጻችን ይከበር ያለበት ታሪካዊ ወቅት ነበር። መምህራን የሕዝብ ድመጽ ይከበር፡ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ይስፈን በማለት ቁመዋል። በዚህም ያመራር  አባላቱ ለእስርና ለስደት ተዳርገዋል።  ዘረኛውም ወያኔ የሕዝብ ድምጽ ሰርቆ “ጠመንጃ በእጇ ስልጣን በደጇ” ብሎ አወጀ።

የኢትየአጵያ ሕዝብ የዲሞክራሲ መብቶቹን ተነጠቀ። መምህራን፡ ባጠቃላይ ሕዝቡም ይመኙት የነበረው ዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ አጣብቂኝ ውስጥ ገባ። በአሁኑ ጊዜ መምህራንን ታግሎ የሚያታግላቸውን ኢመማን መንግስት በተለጣፊዎች አማካይነት ምረኮኛ አድርጎታል።

ወገኖቻችን ልብ በሉ፡፡ እነአሰፋ ማሩ በአደባባይ በጥይት የተገደሉበት፣ መምህር ሺመልስ ዘውዴ የኢመማ ስራ አስፈጻሚ አባልና በኢመማ ስር የተቋቋመው በጡረታ የተገለሉ መምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት መምህር ከበደ ደስታ በእስራት ተንገላተው የሞቱበት፣መምህር ፈቃዱ ፍርዴ፣መምህር ሰርዶ ቶላ በደረሰባቸው እንግልት ለህልፈት ተዳርገዋል.፣በ1999 ኢ,ም ደግሞ የኢመማ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል መምህር አወቀ ሙሉጌታ የአሟሟቱ ምክንያቱ አጠያያቂ መሆኑ የመምህራን መስዋእትነት የከፋ መሆኑን ያመላክታል።  ስንት እልፍ አእላፍ ጀግኖች መስዋእትነት የከፈሉበት የመምህሩ ጉዳይ፣ የትምህርቱ፣የተተኪው ትውልድ መጭ እድል፣የአገር አንድነት፣ የሕዝብ ሉአላዊነት , , , ገና - ገና - ገና ምላሽ ያላገኘ ውስብስብና ጠመዝማዛ የትግል ጉዞ የሚጠይቅ ነው።

ትግል አላማ፣  መነሻና መድረሻ አለው። በሂደቱ የእውቀት፣ የጉልበት፡ የንብረትና የሕይወት መስዋእትነት መጠየቁ አይቀሬ ነው። በዚህ ጽሁፍ ስማቸውን የጠቀስናቸው የኢመማ ሰዎችና ሌሎችም እዚህ ያልተነሱት በርካታዎች ጀግኞቻችን ናቸው። ጀግኖች የወደቁበትን አላማ ማንሳትና ህልው ማድረግ ደግሞ ከሁሉ የበለጠ ጀብዱ ተግባር ይሆናል። በባህላችን፣ በእምነታችን፡በሰብአዊ ተፈጥሮና ባህርይ ለሞተ ማዘን ያለ ቢሆንም ሰብአዊ መብትን፣ ሰብአዊ ክብር በማስጠበቅ መስዋእት የሚሆን ቢሞትም ሕያው ነው።

የሙያ ባልደረባችን መምህር የኔ ሰው ገብሬ  ፍትንና ነጻነት በሌለበት አገር ከመኖር መሞት ይሻላል፡ ስርአቱ ስራ አጥ አድርጎናል፡ ነጻነት ለዳሮ ዋካ ሕዝብ፡ መሪዎቻችን በሙስና ተዘፍቀዋል በማለት ፍትህ ፍለጋ ራሱን በጋዝ አቃጥሎ ተሰዋ። የጀግኖች ጀግና ብንለው ይገባዋል። እኛስ? መችም የመስዋእትነት ዘርፍ ብዙ ነው። በማንኛውም መልኩ መስዋት ለመሆን በሙሉ ፈቃደኝነት የምንዘጋጅበት ወቅት ላይ ነን። ጭቆናን በመቃወምና ጨቋኞችን በመጋፈጥ መስዋእት የሆኑትን ሁሉ እናከብራቸዋለን፣ እናወድሳቸዋለን፣ እንዘከራቸዋለን። የሚጠበቅብንን ብሔራዊ ሃላፊነት ተወጣን የምንለው ግን አርማቸውን አንስተን አንድ እርምጃ ወደፊት ያልን ጊዜ ነው። ያለበለዚያማ በልማድ እንደሚነገረው አጥንታቸው ሊወቅሰን፡ የሞራል ስብራትም አንገት ሊያስደፋን የተመቸን እንሆናለን።

በሃሳብ፡ በትካዜ፡በችጋርና በርሃብ ዋግ እንደመታው ሰብል ጠውልጎ በቁም እየሞቱ መኖርና በመጨረሻም ግብአተ ሞት መድረስ የሕይወት ትርጉም የለውም። የየኔ ሰው ገብሬ መልእክት ይህ በዘር መድሎ ላይ የተመሰረተ ስርአት እንደሰው አልያዘኝም፡እንደባለሙያም ክብሬን አልጠበቀም፡ ስራም አገርም ዜግነትም  ሁሉንም ነገር አሳጥቶኝ መኖር በቃኝ ነው ያለው። ከኛም ይህን ዘረኛ ስርአት በቃ ብለነው ለአካቴው ወደመቃብር እንድናወርድ ይጠበቃል።  የዳሮ ዋካ ሕዝብም ገዥዎቻችን በሙስና የተዘፈቁ ናቸው፡ ነጻነት ለዳሮ ሕዝብ፡ የሕዝብ ድምጽ ይከበር፡ የስራ እድል ተከፍቶ ስራ አጥነት ይቀረፍ፡ የወያኔ አገዛዝ ይብቃ የሚል በየትኛው የአገሪቱ አካባቢዎች ያለነውን ነጸብራቅ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው

ያቀረበው። ይሄው አሁንም የአብራኩ ክፋይ የሆነውን የየኔ ሰው ገብሬን አርማ አንስቶ እያውለበለበው ይገኛል። የነጻነትና የድል ችቦ ሳይበራ ግንባሩን እነደማያጥፍም የሚታየው እንቅስቃሴ አመላካች ነው።

የዳሮ ዋካ ሕዝብ ላቀረበው የመብት ጥያቄ ምላሽ ማጣት ጋር በተያያዘ ራሱን የሰዋው የኔ ሰው ገብሬ ሕልፈት በገዥው አካል ላይ ከፍተኛ ፍርያነትን ቀስቅሷል። የመገናኛ ዘዴዎች ተቋርጠዋል፡ ባጠቃላይ በሕዝቡ ላይ መጠነ ሰፊ ስቃይ እየደረሰበት ስለሆነ በሌሎች ክፍሎች ያሉት ኢትዮጵያውያን ሁሉ ተቋሞአቸውን መግለጽና የትግል አጋርነታቸውን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

**በመጨረሻም የኢመማ ህልውና ከዲሞክራሲያዊ ስእርት መስፈን ጋር በቅጡ የተቆራኘ ስለሆነ ማህበሩን ነጻ ለማውጣት የዲሞክራሲ ስርአት መገንባት ግድ ይላል። በመሆኑም ኢመማ ለዲሞክራሲያዊ ስርአት እውን መሆን አምርሮ ይታገላል።**

ከዚህ በመነሳት፡-

- የኢትዮጵያ መምህራን ባጠቃላይ
- የኢትዮጵያ ሰራተኞች
- አገር ተረካቢ ወጣቶች
- በአገራችሁ የመንግስት ጢሰኛ የሆናችሁ ገበሬዎች
- የሕብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆናችሁ ሴቶች
- የባእድ አገር ሀብታም የበይ ተመልካች የሆናችሁ የንግድ ማህበረሰብ
- የስራ ዋስትና ተነፍጓችሁ እንደ ሎሌ የተቆጠራችሁ የመንግስት ሰራተኞች
- የመንግስት ተቀጥያ ያልሆናችሁ የሃይማኖት አባቶች
- በፍቅርና በመተሳሰብ የኖራችሁ ሙስሊምና ክርስቲያን ምእመናን(አማኞች)
- በውጭ ባገርም ነዋሪ ወገኖቻችን ባጠቃላይ -

አገራችንን ካንዣበባት አደጋ ለመታደግ በአንድነት እንቁም። ይህን ዘረኛና አገር አጥፊ ስርአት እንድንታገል ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

የመምህራንና የኢመማ ትግል ይቀጥላል!

ለበለጠ መረጃ በኢሜይል አድራሻችን ይጠቀሙ፡ eta1941@yahoo.com